የFCPS ታማኝነት ፖሊሲ ዋና ዋና ነጥቦች:

የታማኝነት ፖሊሲው FCPSን ከፌርፋክስ ካውንቲ ፐብሊክ ታማኝነት እና ምስጢራዊነት ፖሊሲ ጋር በማጣጣም፤ የFCPS ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የFCPS ጥቅሞችን እና አገልግሎቶችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለፌደራል ኢሚግሬሽን ባለስልጣናት መረጃ ተላልፎ ይሰጣል ብለው ሳይፈሩ፤ ለሁሉም ተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እና በደስታ የሚቀበል ቦታ ለመስጠት የትምህርት ቤት ቦርዱን ቁርጠኝነት ያረጋግጣል።

ዘርፎች	የFCPS ሰራተኞች እና የስራ አመራሮች ሃላፊነቶች
ሚስጥራዊነትን መጠበቅ	**ሁሉም ሰራተኞች:** • ሁሉንም የተማሪ እና የቤተሰብ ማንነት ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች በተገቢው የFCPS ፖሊሲ እና የቤተሰብ የትምህርት መብት እና የግል መረጃ ህግ (FERPA) በመመርኮዝ ብቻ መረጃን እያስተላለፉ፣ ሚስጥራዊነትን መጠበቅ • የተማሪዎችን ወይም የቤተሰቦቻቸውን ዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታ በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ አለመሰብሰብ ወይም አለመያዝ • የሁሉንም የሰራተኛ መረጃ ሚስጥራዊነት መጠበቅ፣በደንብ 4220 መሠረት ወይም በሌላ ህግ በሚጠይቀው መንገድ ብቻ ማስተላለፍ
ደህንነቱ የተጠበቀ እና በደስታ ተቀባይ አካባቢ መፍጠር	**ሁሉም ሰራተኞች:** • ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደህንነት እና ቤተኛነት የሚሰማቸው መሆኑን ማረጋገጥ እና መዘዞችን ሳይፈሩ መገልገያ አቅርቦት የማግኘት መብታቸውን ማሳደግ • የነጻ እና የቅናሽ ምግብ መርሃግብርን፣ መጓጓዝን እና የትምህርት አሰጣጥን ጨምሮ እና በእነዚህ ብቻ ሳይገደብ፤ በሁሉም የትምህርት ቤት አገልግሎቶች አቅርቦት ሁሉንም ተማሪዎች በእኩልነት መያዝ። • ሁሉም ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ትምህርት ቤትን በደስታ የሚቀበል እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ አድርገው ማየታቸውን ማረጋገጥ
ከዲቪዥን ካውንስል መስሪያ ቤት ጋር መተባበር	**ሁሉም ሰራተኞች:** • የኢሚግሬሽን አስከባሪ ባለስልጣናት ወይም ወኪሎች ለመረጃ ወይም ለመዝገቦች ሁሉንም ጥያቄዎች ለግምገማ ወደ ዲቪዥን ካውንስል መስሪያ ቤት መምራት • ያለ ዲቪዥን ካውንስል መስሪያ ቤት ቅድመ ይሁንታ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢን ለሌሎች ክፍት አለማድረግ።
የጋራ ግንዛቤን ማረጋገጥ	**የስራ አመራሮች:** • በአግባቡ መተግበርን ማረጋገጥ እና ከሰራተኞች እና/ወይም ከማህበረሰብ አጋሮች የሚጠበቁትን ማሳወቅ፤ ሊወሰዱ እና ሊገለፁ የሚችሉ እና የማይችሉ ሚስጥራዊ መረጃዎችን ጨምሮ ማንነትን የሚያሳይ መረጃን ጨምሮ መመሪያዎችን ማካተት። • ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዙ ምርመራዎች እና ለሌሎች ዓላማዎች መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብ፣ እንደሚያዝ እና እንደሚጠበቅ ማብራራት • ተገቢውን የስነ-ስርዓት እርምጃዎችን በመጠቀም የዚህን ፖሊሲ ጥሰቶች መፍታት • ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን የትምህርት ቤት ሪሶርስ ኦፊሰሮች (SROs) የወንጀል ምርመራ በሚያደርጉበት ጊዜ በመደበኛ የትምህርት ቤት የስነ-ስርዓት ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ እንደሌለባቸው እና ይህ መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብ፣ እንደሚጠበቅ እና ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዙ የስነ-ስርዓት ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ምርመራዎች፣ SRO የወንጀል ምርመራ፣ እና ለሌሎች ዓላማዎች እንዴት እንደሚሰበሰብ ማብራራት። • ስልጠና መስጠት እና/ወይም ተዛማጅነት ያለው መረጃ ከሰራተኞች፣ ከውስጥ ባለድርሻ አካላት፣ በወላጅ የሚመሩ ድርጅቶች (እንደ PTAs፣ PTOs፣ ቡስተርስ) እና ማንነትን ሊያሳይ የሚችል መረጃ ሊያገኙ ከሚችሉ ሌሎች የወላጅ እና የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በግልጽ ማጋራት

እንደ FCPS ሰራተኛ፣ የታማኝነት ፖሊሲን በማክበር እና የተገለጹትን ኃላፊነቶች ለመወጣት እያንዳንዳችን ሚና አለን እንዲሁም የጋራ ሃላፊነት እንጋራለን።